January 27 /16

# “ጨዋ” እና “ባለጌ”

(አፈንዲ ሙተቂ)

በዚህ ጽሑፍ ሰዎችን “ጨዋ” እና “ባለጌ” እያሉ የመለየት ልማድ የተፈጠረበትን ታሪካዊ ሂደት እናያለን፡፡

ከአፄ ዓምደ ጽዮን እስከ ዳግማዊ ቴዎድሮስ የነበሩት የኢትዮጵያ ሰለሞናዊ ነገሥታት የነበራቸው ሠራዊት በሁለት ይከፈላል፡፡ በአንደኛው ምድብ የሚካተተው በውጊያ ቴክኒኮችና ታክቲኮች ያልሰለጠነ የገበሬ ጦር ነው፡፡ ይህ የገበሬ ጦር ለውጊያ የሚሰማራው አፄው የክተት ጥሪ በሚያውጅበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ በሌላ ጊዜ እርሻውን እያረሰ በሰላም ይኖራል፡፡ እነዚህ የገበሬ ተዋጊዎች የክተት ጥሪ በሚደረግላቸው ጊዜ ጦርና ጋሻቸውን እየያዙ ነው ወደ ውጊያ የሚመጡት፡፡ ጦር እና ጋሻ የሌለው ገበሬ ደግሞ ሽመል ወይም በትር እየያዘ ለዘመቻ ይሰማራል፡፡

ሁለተኛው ሠራዊት “ጨዋ” ይባላል፡፡ ይህም መደበኛ የአፄው መንግሥት ሠራዊት ማለት ነው፡፡ ይህ የ“ጨዋ” ሠራዊት ለውትድርና ሙያ ብቻ የተቋቋመ ሲሆን የሠራዊቱ አባላት በማንኛውም ወቅት ሌላ ስራ እንዲሰሩ አይፈቀድላቸውም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ አፄው ያለ ቅድመ-ማስታወቂያ ድንገተኛ የውጊያ ትዕዛዝ ሊሰጣቸው ስለሚችል ነው፡፡ ስለዚህ የሠራዊቱ አባላት ምንጊዜም ቢሆን ለውጊያ ዝግጁ ሆነው መገኘት አለባቸው፡፡

የ"ጨዋ" ሠራዊት በክፍለ ጦር ደረጃ የተዋቀረ ሲሆን እያንዳንዱ ክፍለ ጦር የእግረኛ፣ ቀስተኛ እና ፈረሰኛ ክፍሎች ነበሩት፡፡ እነዚህ የጨዋ ክፍለ ጦሮች መኖሪያቸውን የሚቀልሱት ከአፄው በተመደቡበት ግዛት ነው፡፡ ማንኛውም ክፍለ ጦር ከአፄው እውቅና ውጪ ከመኖሪያ ግዛቱ መንቀሳቀስ አይችልም፡፡ በአጎራባች ግዛቶች ውጊያ ቢቀሰቀስ እንኳ ያለ አፄው ትዕዛዝ ውጊያውን አይቀላቀልም፡፡ የጨዋ ሠራዊት ተግባራት ሁለት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ተግባር ከአፄው ትዕዛዝ በሚመጣለት ጊዜ ከንጉሡ ጋር ለውጊያ መሰማራት ነው፡፡ ሁለተኛው ተግባሩ ደግሞ የተመደበበትን ግዛት ጸጥታና ደህንነት መጠበቅ ነው፡፡ በግዛቱ አንዳች የአመጽ ንቅናቄ ቢከሰት የሠራዊቱ አዛዥ የአፄውን ትዕዛዝ ሳይጠብቅ "ጨዋ"ዎችን አዝምቶ አመጹን እንዲጨፈልቀው ስልጣን ተሰጥቶታል። አዛዡ እና ሠራዊቱ በዚህ ደምሳሽ ተግባር ለሚደርሰው ጥፋትና ውድመት ተጠያቂ አይሆኑም፡፡ ይሁንና የጨዋ ሠራዊት በአፄው መንግሥት ልዕልና ላይ አደጋ የማያስከትሉ የወንጀል ድርጊቶችን አይከታተልም፡፡ ይህንን ፖሊሳዊ ተግባርና የፍርድ ጉዳዮችን የሚፈጽመው የግዛቱ አስተዳደር ነው፡፡

የጨዋ ሠራዊት አባል የሆነ ወታደር ሁለት የገቢ ምንጮች ነበሩት፡፡ የመጀመሪያው በውጊያ ጊዜ የሚያገኘው ዘረፋ እና ምርኮ ሲሆን በውጊያው ድል ካደረገም አፄው ተጨማሪ ሽልማቶችን ሊሰጠው ይችላል፡፡ የጨዋዎች ሁለተኛ የመተዳደሪያ ምንጭ ደግሞ በሚሰፍሩባቸው ግዛቶች ውስጥ የሚሰጣቸው መሬቶች ናቸው፡፡ እነዚህ መሬቶች “ጉልት” ይባላሉ፡፡ የ“ጉልት” መሬት በክፍለ ግዛቱ ለሚመደቡት ጨዋ ወታደሮች የአገልግሎት ክፍያ ሆኖ እየታሰበ ለያንዳንዱ ወታደር በነፍስ ወከፍ የሚሰጥ ነው፡፡ በዘመኑ ደንብ መሠረት የመሬቱ ባለቤት የክፍለ ግዛቱ ነባር ገበሬ ነው፡፡ ይህ ገበሬ ነባር መሆኑን ለማመልከት “ባላገር” (ባለ ሀገር) እየተባለ ይጠራ ነበር፡፡ “ባላገር” በመሬቱ ላይ ያለውን የባለቤትነት መብት አያጣም፡፡ ነገር ግን በዓመቱ መጨረሻ ላይ ከሚያገኘው ምርት አንድ ሦሥተኛውን የርሱ ተጓዳኝ ሆኖ ለሚመደበው “ጨዋ” ወታደር ማስገባት አለበት (ይህ ክፍያ በየዓመቱ ለሲቪሉ አስተዳደር ከሚከፈለው ግብር ጋር አይደመርም)፡፡ በተጨማሪም “ባላገሩ” ለጨዋው የጉልበት አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ተጥሎበታል፡፡

የጨዋ ወታደሮችን በዚህ መንገድ ከባላገር ገበሬው ጋር ማጣመር ያስፈለገው ጨዋው መሬቱን በራሱ የሚያርስበት ጊዜ ስለማይኖረው ነው- ይላሉ የዘመኑን ሁኔታ የሚስረዱ ሰነዶች፡፡ ምክንያቱም ደግሞ -ከላይ እንደገለጽኩት- ጨዋው በየትኛውም ጊዜ የውጊያ ጥሪ ሊደረግለት ስለሚችል ነው፡፡ ታዲያ ይህ በእኩልነት ላይ ያልተመሰረተ የ“ባላገር” እና የ“ጨዋ” ጥምረት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ለተነሱት ፖለቲካዊና ማህበራዊ ውጥንቅጦች መንስዔ ሊሆን በቅቷል፡፡

በዚህ ጽሑፍ ሁሉንም ለማውሳት አይቻልም፡፡ ከዚያ ይልቅ የዚያ ጥንታዊ “የጨዋ” እና “ባላገር” ጥምረት ማስታወሻ ሆኖ የቀረውን ውርስ (legacy) ብቻ እዳስሳለሁ፡፡

*****

“ጨዋ” በመሠረቱ “መደበኛ ሠራዊት” ማለት ነው ብያችኋለሁ፡፡ ይሁንና ይህ ቃል በዚህ ዘመን ፍቺውን ቀይሮ “ጥሩ ምግባር ያለው” በሚል አገባብ እያገለገለ ነው፡፡ በዘመናችን ለ“ጨዋ” ተቃራኒ ትርጉም የሚሰጠው ደግሞ “ባለጌ” የሚለው ቃል ነው፡፡ ሰዎችን በነዚህ ሁለት ተቃራኒ ቃላት መጥራቱ ከየት እንደመጣ አውቃችኋልን?…

የታሪክ ምሁሩ ፕሮፌሰር መርእድ ወልደ አረጋይ እንደሚሉት “ባለጌ” ከጥንቱ “ባለሀገር/ባላገር” ተለውጦ (corrupted ሆኖ) የተፈጠረ ቃል ነው፡፡ ይህ ቃል “ጨዋ” ከሚለው ቃል ጋራ ፍፁም ተቃራኒ የሆነ ትርጉም ሊያገኝ የቻለው “ባላገር” እና “ጨዋ” በተባሉት የጥንቱ ተጣማሪዎች መካከል በነበረው አቻ ያልሆነ ጉድኝት መነሻነት ነው፡፡ “ጨዋ” ወታደር እና “ባላገር” ገበሬ በጅምሩ ላይ ኢኮኖሚያዊ ጉድኝት ብቻ ነው የነበራቸው፡፡

እያደር ግን በሁለቱ መካከል ማህበራዊ ልዩነቶችን የሚፈጥሩ ደንቦች በስራ ላይ ዋሉ፡፡ በአንድ ወቅት ባላገሩ “ላቤን አንጠፍጥፌ ያፈራሁትን ለጨዋ ወታደር አልሰጥም” ብሎ በማመጹ የጦር መሳሪያ እንዳይይዝ ተከለከለ፡፡ በየጊዜው አመጹን አላቆም እያለ በማስቸገሩም ሌሎች ደንቦች ተደነገጉ፡፡ በዚህም መሰረት ከገዥዎች ፈቃድ ውጪ በሬ እንዳያርድ እና ጥሩ ዋጋ የሚያወጡ ልብሶችንም እንዳይለብስ ተደረገ፡፡ በገዥዎች ካልተፈቀደለት በስተቀር ቤትና አጥር እንዳይሰራም ተከለከለ፡፡ ይህም በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በነበሩ ህዝቦች መካከል የመደብ ልዩነትን ፈጠረ፡፡ ከስርዓቱ ጋር በጥብቅ የተቆራኘው መደብ “ጨዋ” ተባለ፡፡ የዚህ “ጨዋ” አገልጋይ የሆነው መደብ ደግሞ “ባለጌ” እየተባለ መጠራት ጀመረ፡፡

ይህ የፕሮፌሰር መርዕድ ትንተና በሌሎች ምንጮችም የተረጋገጠ በመሆኑ በመደቦቹ አፈጣጠር ላይ ጥያቄ አይነሳም፡፡ "ባለጌ" የሚለውም ቃልም ፕሮፌሰር መርዕድ እንዳሉት "ባላገር" ከሚለው ቃል ተለውጦ የተፈጠረ ሊሆን ይችላል፡፡ "ባላገር" የሚለው ቃል

እስከ ዘመናችን ድረስ በአገልግሎት ላይ ያለ መሆኑን ስናስተውል ግን "ባለጌ" ከ"ባላገር" መገኘቱን እንጠራጠራለን፡፡ የዚህም ምክንያት ለ"ባለጌ" መነሻ ነው ተብሎ የተነገረን "ባላገር" ከላይ ከገለጽነው ታሪክ ጋር የማይገናኝ ፍቺን ይዞ በአማርኛ ቋንቋ በማገልገል ላይ መሆኑ ነው፡፡

ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት "ባላገር" ብዬ የጠራሁት የጨዋ ወታደር ተጓዳኝ በኋለኛው ዘመን "ጭሰኛ" እየተባለ ሲጠራ የነበረው ገባር ገበሬ አምሳያ ነው፡፡ ጭሰኛ አሉታዊ ስሜት የሚሰጥ ቃል ነው፡፡ ባላገር ግን ዛሬም ድረስ "የገጠር ሰው" የሚል ፍቺ ነው ያለው፡፡ ይህ ትርጓሜ በምንም መልኩ አሉታዊ ስሜት የለበትም፡፡ ባላገር ከጭሰኛ ጋር የሚቀራረብ አገልግሎት የነበረው ቢሆን ኖሮ በዘመናችን አዎንታዊ ስሜትን በሚሰጥ መልኩ ባላገለገለ ነበር ባይ ነኝ፡፡

"ባለጌ" እና "ባላገር" በዚህ ዘመን ሐራምባ እና ቆቦ የሆኑ ፍቺ ነው ያላቸው፡፡ "ባለጌ" ከባላገር የተገኘ ቢሆን ኖሮ ቃላቱ መሳ ለመሳ አገልግሎት ይሰጡ ነበርን?… እንደሁኔታው ነው፡፡ ይሁን እንጂ አንድ ቃል በዘመናት ሂደት እየተጣመመ እና እየተሸራረፈ ቅርጹ የሚለወጥ ከሆነ በአዲሱ ቅርጽ ለብቻው አገልግሎቱን ይቀጥላል እንጂ ከጥንታዊው (ኦሪጂናሌው) ቃል ጋር ጎን ለጎን ሆኖ የሚያገለግልበት ክስተት እምብዛም አይስተዋልም፡፡ ለምሳሌ "ባላምባራስ" (ባለ አምባ ራስ)፣ ሻምበል (የሺህ አምበል)፣ ዣንጥላ (ዣን ጥራር) የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ይህንን ሁሉ የምለው ለምን መሰላችሁ?…. "ባለጌ" የሚለው ቃል የተገኘበት ኦሪጂናሌ ቃል እና በዚህ ቃል ይጠሩ በነበሩት ዜጎች ላይ የተጣሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እቀባዎች እያደጉ የሄዱበት መንገድ በሌላ አቅጣጫ ሊታወቁ የሚችሉ ስለመሰለኝ ነው፡፡ በኔ ድምዳሜ መሰረት "ባለጌ" የሚለው ቃል "ባላገር" ከሚለው የተወረሰ አይደለም፡፡ ጨዋ ወታደሮችን የሚያገለግል ጭሰኛ ሆኖ ሲመደብ የነበረው ያ የጥንቱ ገባር መጠሪያ "ባለ ጌይ" ወይንም "ባለ ቀዬ" እንደሆነ ነው የማምነው፡፡

"ጌይ" በኢትዮ-ሴማዊ ቋንቋዎች ውስጥ ሀገር፣ መንደር፣ ወይንም ከተማ እንደማለት ነው፡፡ ቃሉ በሀረሪ፣ ሲልጢ፣ ጉራጊኛ ወዘተ ውስጥ እስከ አሁን ድረስ አለ፡፡ በትግርኛ ውሥጥም የነበረ ይመስለኛል፡፡ ለዚህም አብነት የሚሆነው በዛሬው ትግራይ ክልል ውስጥ "እስማላ ጌይ"፣ "አላጌ"፣ "ሐሸንጌ" ወዘተ… እየተባሉ የሚጠሩ መንደሮች መኖራቸው ነው፡፡ በጎንደር ከተማ አቅራቢያ ደግሞ "እስላምጌ/እስላም ጌይ" የሚባል መንደር አለ፡፡ ሆኖም የአማርኛው "ጌይ" በታሪክ ሂደት ወደ "ቀዬ" የተለወጠ ይመስለኛል፡፡

እንግዲህ በዚህ ምልከታችን መሰረት የጥንቱ ጭሰኛ ገበሬ "ባለ ጌይ" እየተባለ ይጠራ ነበር ማለት ነው፡፡ ይህም "የሀገሩ ሰው"፣ "ነባር ነዋሪ" ወይንም "ባለመሬቱ" እንደማለት ነው፡፡ ይህ "ባለ ጌይ" ነበረ ምርቱን ከጨዋ ወታደር ጋር እንዲካፈል የተገደደው፡፡ ገበሬው በጨዋ ወታደር የሚደርስበት ብዝበዛ ሲመርረው ከብዝበዛው ለመገላገል አመጽ መሞከር ጀመረ፡፡ ጨዋዎች አመጹን እየቀለበሱት ገበሬውን መበዝበዛቸውን ቀጠሉ፡፡ በልዩ ልዩ ግዛቶች የአመጽ ሙከራዎች ሲበረክቱ ደግሞ ገበሬው የጦር መሳሪያ እንዳይታጠቅ በአዋጅ ተከለከለ፡፡ እያደርም ከላይ የተገለጹት የገበሬውን ስነ-ልቦና የሚያላሽቁ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እቀባዎች በገባሩ ገበሬ (ባለጌይ) ላይ ተጣሉ፡፡

እነዚህም እርምጃዎች የሀገሪቱን ህዝብ ለሁለት የከፈሉ መደቦች እንዲፈጠሩ አደረጉ፡፡ ለገዥው ክፍል ቅርብ የሆነው ወገን "ጨዋ" ተባለ፡፡ ገባሩ ክፍል ደግሞ "ባለጌይ" (ባለጌ) ተብሎ መጠራቱን ቀጠለ፡፡ "ጨዋው" ለአፄው ህግ ታማኝና ተገዥ ተደርጎ ስለሚታሰብ በስነ-ምግባሩም ጭምር ከሌላው መደብ የሚበልጥ ሆኖ ተወሰደ፡፡

"ባለጌይ" ግን በየጊዜው ስለሚያምጽ በኢኮኖሚው በኩል ከነበረው የበታችነት በተጨማሪ ለስርዓት የማይገዛ ምግባረ ብልሹ መደብ ተብሎ ተፈረጀ፡፡ ያ ጥንቱ የሠራዊት አደረጃጀት እና የኢኮኖሚ አወቃቀር ቀስ በቀስ ሲጠፋ ደግሞ "ጨዋ" እና "በለጌይ" የግብረ ገብነት መግለጫ ቃላት ሆነው ቀጠሉ፡፡ እነሆ እኛም ቃላቱን ወርሰን "ጨዋ" እና "ባለጌ" እያልን እንገኛለን፡፡